አይኖረውም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት ቀደም ሲል በተሰጠው ውሣኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ቀርቦበታል በሚል ምክንያት እንደገና ዳኝነት ሊታይ አይችልም በሚል በሰጠው ብይን ተፈጽሟል የሚባል የሕግ ስህተት የለም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ በፍ/መ/ቁ.3324, ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡



የሰበር መ.ቁ. 16720

ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ተገኔ ጌታነህ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ት አበራሽ ጉቱ

መልስ ሰጭ፡- 1. የመካከለኛው አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት

2. አቦቦ እርሻ ልማት ድርጅት

3. ተንዳሆ እርሻ ልማት ድርጅት

4. የሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅት

*ፍርድ እንዲፈጸም ስለማቀርብ ማመልከቻና ስለ አፈፃፀሙ ስነስርዓት - ለፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት - ጉድለት ያለበት የፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻ ተስተካክሎ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ*

*ስለማስጥበት ስርዓት፡- የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 378፣ 384፣ 385/1/*

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መ/ሰጭዎች ለአመልካች ብር 167,831.94 እንዲከፍሉ፤ አመልካች በበኩላቸው ለመ/ሰጭዎች ብር 17,183.94 እንዲከፍሉ፤ ከሰጠው ውሳኔ አመልካች ለመ/ሰጪ ብር 17,182.50 እንዲከፍሉ የተሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመለወጥ የተጠቀሰውን ገንዘብ/ብር 17,182.50/ መ/ሰጭዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ በመወሰኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ከመስጠቱ ቀደም ብሎ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሲሰጥ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍሉ የተወሰነውን እና በጠቅላይ ፍ/ቤቱ በኋላ የተሻሻለውን ብር 17,182.50 ቀንሰው ቀሪውን ገንዘብ ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ የተሰጠው ትእዛዝ እንዲስተካከልና በዋናው ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲከፈል ትዕዛዝ እንዲሰጥ በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ አመልካች የጠቅላይ ፍ/ቤትን ውሳኔ ባለማያያዙ በውሳኔው መሠረት ትእዛዝ ሂሳብ ሲሰራ ይችል ስላልነበርና በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፍል የተሰጠ ውሣኔ ባለመኖሩ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ የሰጠው ትዕዛዝ ትክክል ነው በሚል ውድቅ በማድረጉና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ውሳኔውን በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

**ውሳኔ፡-** የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

1. በአንድ ውሣኔ ላይ በከፊል ባለመብት የሆነ ተከራካሪ ወገን ባለመብት የሆነበት የውሳኔ ክፍል እንዲፈጽም ማመልከቻ ከማቅረብ የሚከለክለው ነገር የለም፡፡
2. የአፈፃፀም ማመልከቻው የቀረበለት ፍ/ቤትም ውሳኔው ካልታገደ በቀር አፈጻጸሙን ሊቀጥል ይገባዋል፡፡
3. ከፊል ባለመብት የሆነ ተከራካሪ ወገን ከፊል ባለመብት የሆነበት የውሳኔ ክፍል እንዲፈጸምለት የአፈፃፀም መዝገብ ከፍቶ ከፊል ባለዕዳ በሆነበት የውሳኔ ክፍል ይግባኝ ካቀረበና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ባዩን የሚጠቅም ውሳኔ ከሰጠ ባለመብቱ አዲስ የአፈጻጸም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው፤ ሌላ የአፈጻጸም ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ የቀድሞው የአፈጻጸም መዝገብ እንዲንቀሳቀስ እና የተሻሻለው ውሳኔ እንዲፈጸምለት ለማድረግ ይችላል፡፡

4. የመጀመሪያው የአፈጻጸም ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ ተፈጽሞ ያለቀ ቢሆንም እንኳን የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው በቀድሞው የአፈጻጸም መዝገብ ላይ እንዳይቀጥል የሚከለክል ምክንያት የለም፡፡

5. የአፈጻጸም መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ የቀረበው ጥያቄ ትክክል ያልሆነ ህግ ተጠቅሶ የቀረበ ቢሆንም እንኳን ማመልከቻው እንዲስተካከል ፍ/ቤቱ ያዛል ወይም ፍ/ቤቱ ራሱ አግባብነት ያለውን ህግ መሰረት አድርጎ ጥያቄውን ይመረምራል እንጅ ማመልከቻውን ውድቅ ማድረግ አይገባም፡፡

6. በአፈጻጸም ደረጃ ወለድ እንዲከፈል ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መስጠት የሚችለው በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፈል ውሳኔ ከተሰጠ ነው፡፡



መ/ቁ. 16720

ጥቅምት 22 ቀን 1998

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ተገኔ ጌታነህ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሒሩት መለሰ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አበራሽ ጉቱ ወኪል ሚደቅሳ ጉቱ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. የመካከለኛ አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት - አልቀረቡም፡፡

2. አቦቦ እርሻ ልማት ድርጅት አልቀረቡም፡፡

3. ተንዳሆ እርሻ ልማት አልቀረቡም፡፡

4. የሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅት - አልቀረቡም፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የአሁኑ አመልካች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በ07/7/93 ጽፈው ያቀረቡትን የአፈፃፀም ማመልከቻ መሠረት በማድረግ ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለሥር ፍ/ቤት በፃፉት አቤቱታ

የአሁኑዎቹ ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 167831.94 /አንድ መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከዘጠና አራት ሳንቲም/ እንዲከፍሉ ሲወስንባቸው በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ለተጠሪዎች ብር 17182.50 /አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሁለት ብር ከሀምሳ ሳንቲም/ እንዲከፍሉ ወስኖባቸዋል፡፡ ሆኖም አመልካች ለተጠሪዎቹ እንዲከፍሉ የተወሰነውን ገንዘብ በተመለከተ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ውሣኔው የተሻረ በመሆኑ ቀደም ሲል ፍ/ቤቱ የአፈፃፀም ትእዛዝ ሲሰጥ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍሉ የተወሰነውን ብር 17182.50 ቀንሶ ቀሪውን ገንዘብ ብቻ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ የሰጠውን ትእዛዝ እንዲያስተካክል እና እንዲሁም በዋናው ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲከፈል ትእዛዝ እንዲሰጥ አመልክተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም አቤቱታውን መርምሮ ለአፈፃፀም መሠረት በሆነው በመ/ቁ 639/82 ሐምሌ 30 ቀን 1983 ዓ.ም በተሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀም የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲቀርብ አመልካች የጠቅላይ ፍ/ቤትን ውሣኔ ከመዝገቡ ጋር ስላላያያዙ ፍ/ቤቱ የአፈፃፀም ትእዛዝ



የሰጠው በዚሁ ውሣኔ መሠረት ሲሆን ትእዛዝ በተሰጠበት ወቅት ፍ/ቤቱ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ መሠረት በማድረግ ሂሣቡን ሊሰራ ስለማይችል የሰጠው ትእዛዝ ትክክለኛ ስለሆነ የሚታረም አይደለም፣ በተፈረደው ገንዘብ ላይም ወለድ እንዲከፈል የተሰጠ ውሣኔ ስለሌለ የወለድ ይከፈለኝ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም የፌ/መ/ደ/ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታም የጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ለተጠሪዎች ብር 17182.50 እንዲከፍሉ የተሰጠውን ውሣኔ በመሻር ይህንኑ ገንዘብ ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ የሰጠውን ውሣኔ የሥር ፍ/ቤት እንዲፈፀም ትእዛዝ አለመስጠቱ የተሰጠውን ውሣኔ የሚለውጥ ወይም የሚሽር ስለሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ስለዚህ ገንዘብ እንዲከፈለኝ እና በዋናው ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲከፈለኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎችም የአመልካች የሰበር አቤቱታ ደርሷቸው በሰጡት መልስ ቀደም ሲል አመልካች በመ/ቁ 639/82 ሐምሌ 30/1983 በተሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀምላቸው የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበው በውሣኔው መሠረት ተፈጽሞ ጉዳዩ አብቅቷል፡፡ በወቅቱ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ከአፈፃፀም ማመልከቻው ጋር አያይዘው አላቀረቡም፡፡ ስለዚህ አዲስ አፈፃፀም መዝገብ ከሚከፍቱ በቀር የጠቅላይ ፍ/ቤቱን ውሣኔ መሠረት አድርገው የቀድሞ አፈፃፀም ትእዛዝ እንዲስተካከል ያቀረቡት ጥያቄ ሥነ-ሥርዓትን ያልተከተለ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

ከላይ የተመለከተው የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን በዚህም ጉዳይ ሊታይ የሚገባው ነጥብ አንድ ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርብ ማመልከቻን የአቀራረብ እና የአፈፃፀም ሥርዓት ነው፡፡

አንድ የአፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት የሚጀምረው የተፈረደለት ሰው /የፍርድ ባለመብት/ በፍርዱ መሠረት እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም



ማመልከቻ ለፍ/ቤቱ ሲያቀርብ ነው /የሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378/1/ ይመለከቷል/፡፡ በመሆኑም አንድ የአፈፃፀም ማመልከቻ ከማቅረቡ በፊት የተፈረደ ፍርድ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ እንዲፈፀም በሚቀርበው የፍርድ ውሣኔ ደግሞ ከሳሽ ከጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ ውስጥ ከፊሉ ተወስኖለት ከፊሉ ውድቅ የሚደረግበት ወይም በከፊል አንደኛው ተከራካሪ ወገን በከፊል ደግሞ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ባለመብት ሊሆኑ የሚችሉበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ በመሆኑም በከፊል ባለመብት የሆነው ወገን ወይም ከፊል የዳኝነት ጥያቄው ውድቅ የተደረገበት ወገን በተወሰነበት ጉዳይ ወይም ውድቅ በተደረገበት የዳኝነት ጥያቄ ላይ ይግባኝ ጠይቆ በተፈረደለት መጠን ብቻ የአፈፃፀም ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይግባኝ የተባለበት ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ ሲያገኝ ባለመብቱ አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው አዲስ የአፈፃፀም ማመልከቻ በማቅር ብቻ የቀድሞውን የአፈፃፀም መዝገብ ከማንቀሳቀስ የሚከለክለው ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይ የሚለው በዚህ ጉዳይ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ነው፡፡

በመሠረቱ የአፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት ዓላማው በአንድ ውሣኔ ወይም ትእዛዝ ባለመብት የሆነውን ሰው ውሣኔው ወይም ትእዛዙ ያስገኘለት መብት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ በመሆኑ አንድ ፍ/ቤት ሊፈፀም የሚችል ውሣኔ እስከቀረበለት ድረስ ውሣኔው እንዲፈፀም ተገቢውን ትእዛዝ መስጠት ይገባዋል፡፡ በመሆኑም በአንድ ውሣኔ ላይ ከፊል ባለመብት የሆነ ተከራካሪ ወገን ባለመብት የሆነበት የውሣኔ ክፍል ሊፈፀም የሚችል እስከሆነ ድረስ ይኸው የውሣኔ ክፍል እንዲፈፀም ማመልከቻ ከማቅረብ የሚከለክለው ነገር የለም፡፡ የአፈፃፀም ማመልከቻ የቀረበለት ፍ/ቤትም፣ ውሣኔው ካልታገደ በቀር አፈፃፀሙ ሊያቆም ስለማይችል /የሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 332 ይመለከቷል/፣ አፈፃፀሙን ሊቀጥል ይገባዋል፡፡ ይግባኝ የተባለበት ከፊል የውሣኔው ክፍል ግን ሊፈፀም የሚችለው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ የመሻር፣ የመለወጥ፣ ወይም የማሻሻል ስልጣን አለውና ነው፡፡ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ባዩን የሚጠቅም ውሣኔ ከሰጠ ባለመብቱ፣ አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት



ሳያስፈልገው፣ ሌላ የአፈፃፀም ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ የቀድሞ የአፈፃፀም መዝገብ እንዲንቀሳቀስ እና ውሣኔው እንዲፈፀምለት ለማድረግ ይችላል፡፡ የመጀመሪያው የአፈፃፀም ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ ተፈጽሞ ያለቀ ቢሆንም እንኳን የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በቀድሞው መዝገብ ላይ እንዳይቀጥል የሚከለክል ነገር የለም፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 378/3/ረ/ እና ቁጥር 384ም አንድ የአፈፃፀም ማመልከቻ ከቀረበ በኋላ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በተለያየ ጊዜ ሌላ ማመልከቻ እየቀረበ ነገሩን ለማንቀሳቀስ እንደሚቻል ማመልከታቸው ባለመብቱ አዲስ መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በቀድሞ መዝገብ እንዲፈፀም ማድረግ የሚቻል መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ የዚህም አላማ በአንድ ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በአንድ መዝገብ ተጠቃሎ እንዲፈጸም ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህም በከፊል የውሣኔው ክፍል ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ያቀረበ ወገን ይግባኝ ያለበት ጉዳይ እስኪወሰን ሳይጠብቅ የፍርድ ባለመብት የሆነበት ጉዳይ ብቻ እንዲፈፀም ሊያመለክት ይችላል፡፡ ይግባኝ ያለበት ጉዳይ ከተወሰነለት ደግሞ አዲስ

መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው ሌላ የአፈፃፀም ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ የቀድሞውን መዝገብ አንቀሳቅሶ በይግባኝ የተወሰነለትን ፍርድ ሊያስፈጽም ይችላል፡፡

ከዚህ በመነሳት ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በመ/ቁ. 639/82 በ30/11/83 የከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ተጠሪዎች ለአመልካች 163529 ብር እና የዳኝነቱን ገንዘብ እንዲከፍሉ ሲወስን አመልካች ደግሞ ለተጠሪዎች 17182.50 ብር ከነዳኝነቱ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ በመ/ቁ. 657/84 በ26/9/84 በዋለው ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሣኔ በመለወጥ 17182.50 ብር ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በመሆኑም አመልካች በከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲከፈላቸው ከተወሰነላቸው ብር 163529 በተጨማሪ ብር 17182.50 እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡

ነገር ግን አመልካች የመጀመሪያ የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርቡ እንዲፈጸምላቸው የጠየቁት በመ/ቁ. 639/82 የተሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ በወቅቱ የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፈጸም የቀረበ ጥያቄ አልነበረም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት



እንዲፈፀም የሰጠው ትእዛዝ ትክክል ነበር፡፡ ነገር ግን አመልካች ይግባኝ ለጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው አስወስነዋል፡፡ በመሆኑም አዲስ መዝገብ መክፈት ሳያስፈልጋቸው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈጸምላቸው ሌላ የአፈፃፀም ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ ጉዳዩ እንዲንቀሳቀስላቸው መጠየቃቸው የሥ/ሥ/ሕጉ የሚፈቅድላቸው ነው፡፡ በእርግጥ አመልካች ማመልከቻውን ሲያቀርቡ የጠየቁት የአፈፃፀም ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320 እና 208 መሠረት እንዲያስተካክል በመሆኑ ለጥያቄአቸው መሠረት ያደረጓቸው የሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው ቢሆንም አንድ ባለጉዳይ አቤቱታውን ለፍ/ቤቱ ሲያቀርብ ሕግ የመጥቀስ ኃላፊነት የሌለበት በመሆኑ አመልካች የተሳሳተ የሕግ አንቀጽ በመጥቀሳቸው ብቻ አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ አይገባም፡፡ የቀረበለትን ማመልከቻ አግባብነት ካለው የሕጉ ድንጋጌ ጋር መመርመር ተገቢውን መፈፀም የፍ/ቤቱ ኃላፊነት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ የአፈፃፀም ማመልከቻው በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት አልቀረበም የሚልበት ምክንያት ካለው እንኳን አቤቱታው ተስተካክሎ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል /የሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 385/1/ ይመለከቷል/፡፡

አመልካች በይግባኝ ፍ/ቤት የተሰጣቸውን ፍርድ ለፌ/መ/ደ ፍ/ቤት ስላቀረቡ ፍ/ቤቱ ውሣኔው መሠጠቱን አውቋል፡፡ ስለዚህም በውሣኔው መሠረት እንዲፈፀምላቸው ተገቢውን ትእዛዝ ከመስጠት ፋንታ አመልካቹ የተጠቀሱት የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ በመሣሣቱ ብቻ አቤቱታውን ውድቅ በማድረጉ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

ሌላው አመልካች የጠየቁት በተፈረደው ዋና ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲከፈላቸው ነው፡፡ በርግጥ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378/3/ሰ/ የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲቀርብ በፍርዱ መሠረት የሚጠየቀው የገንዘብ ልክ ከነወለዱ እንዲገለጽ ያዛል፡፡ ነገር ግን ይህ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ በዋናው ውሣኔ ላይ ወለድ እንዲከፈል የተሰጠ ውሣኔ ካለ ይኸው ወለድ ተሰልቶ ትክክለኛው አሀዝ በአፈፃፀም በማመልከቻው እንዲገለጽ የሚያዝ እንጂ ውሣኔ ያልተሰጠበትን የወለድ ክፍያ የአፈፃፀም ፍ/ቤቱ እንዲያስከፍል ስልጣን የሚሰጠው አይደለም፡፡ ምክንያቱም አንድ የአፈፃፀም ፍ/ቤት በውሣኔው መሠረት ከማስፈፀም አልፎ ውሣኔ ያልተሠጠበትን ጉዳይ እንዲፈፀም የማድረግ ስልጣን የለውም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ በሰጡት ውሣኔ ላይ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚባልበት ምክንያት የለም፡፡



## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 103/90 በመጋቢት 20 ቀን 1993 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 8076 በግንቦት 17 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪዎች ብር 17182.50 /አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ብር ከሃምሣ ሳንቲም/ እና የዳኝነቱን ብር 671.00 /ስድስት መቶ ሰባ አንድ/ በድምሩ 17853.50 /አስራ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሣ ሦስት ብር ከሃምሣ ሳንቲም/ ለአመልካች ይክፈሉ፡፡
3. አመልካች በጠየቁት የገንዘብ መጠን ብር 17182.50 /አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሁለት ብር ከሃምሣ ሳንቲም/ ወለድ ሊከፈላቸው አይገባም፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡